# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 78 ህዳር 3 2002 ዓ.ም


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ፍትህ ዝም ብሎ ቁጭ ብለው ስላዩት ወይም ስለፈለጉት የሚመጣ ነገር አይደለም። ፍትህዊ ስርአትን ማምጣት ትግልን ይጠይቃል። በእስር ቤት ያላችሁ ለፍትህ ብላችሁ የታገላችሁና ለነጻነታችው ሲሉ የተሰውት ቤተሰቦች ሁሉ ፡ የእናንተ ስቃይ የእናንተ ሰቆቃ እንዲሁም የሞቱት ወገኖቻችን መስዋትነት ተደማምሮ ነው ያንን ነጻነት የሚጠን የሞቱትም ደማቸው ደመከልብ ሆኖ አይቀርም። አንድ ቀን ስማቸው በክብር ይዘከራል፣ በእስር የምትሰቃዩትም የጊዜ ጉዳይ ነው እንጅ ያች የታገላችሁላት ፍትህ ያች የታገላችሁላት ነጻነት እንደምታዩዋት አረጋግጥላችዋለሁ ዶ/ር ብርሓኑ ነጋ

## የመለስ ዜናዊ የሰብአዊ መብት አያያዝ እጅግ እየተበላሸ መሆኑን አንድ ባለስልጣን ተናገሩ

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የሰብአዊ መብት አያያዝ ሪኮርድ እጅግ እየተበላሸ በሄደ ቁጥር ከምዕራብ አገሮች የሚያገኘው እርዳታ እየጨመረ መምጣቱ እጅግ አሳሰቦናል ሲሉ የሂውማን ራይትስ ዎች የአፍሪካ ዳይረክተር ተናገሩ።

ዳይረክተሩ ሚስተር ጆናታን ኤልዮት ይህንን የተናገሩት ተቀማጭነቱ በቤልጅዬም አገር በብራስልስ ከተማ የሆነ በአውሮፓ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ አማካሪ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት በአፍሪካ ቀንድ የዲሞክራሲና የሰብዓዊ መብት አያያዝ ላይ አውሮጳና አሜሪካ የተቀናጀ ፖሊሲ እንዲከተሉ ለማወያየት ባለፈው ሰኞ ጥቅምት 30 እና በማግስቱ ማክሰኞ ህዳር አንድ ቀን 2002 ባዘጋጀው ስብሰባ ሂውማን ራይትስ ዎችን ወክለው ስለ ክልሉ የመብት ጥሰት ምስክርነት በሰጡበት ወቅት መሆኑን ስብሰባውን የተከታተለው የግንቦት 7 ዘጋቢ ከላከልን ዜና ለመረዳት ተችሎአል።

በአፍሪካ ቀንድ ካሉት አገሮች በህዝብ ብዛቷ የመጀመሪያው በሆነቹው ኢትዮጵያ የሚፈጸመው የሰበአዊ መብት ጥሰት እጅግ ዘግናኝ እንደሆነ ሂውማን ራይትስ ዎች ተጨባጭ መረጃዎች ለአሜሪካና አውሮጳ መንግስታት አቅርቦአል ያሉት ዳይሬክተሩ ሚስቴር ኤልዮት፤ የአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር የሆነቹውን ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን ጨምሮ አጅግ በርካታ ዜጎች በፖለቲካ እምነታቸው ምክንያት ብቻ በእስር ላይ እንደሚገኙ ፤ በኦጋዴን እየተካሄደ ያለው ሰቆቃ አሁንም እንዳልተገታ ፡ ገለልተኛ የሆነ አለም አቀፍ መርማሪ ኮሚሽን አስከዛሬም ወደ ቦታው እንዳልተላከ ከዘረዘሩ በኋላ የኤርትራን መንግስት የሰብአዊ መብት ሪኮርድ የተቹት የቀድሞው የአሜሪካ አምባሳደር ሮበርት ሁዑደክ (Robert G. Houdek) ስለኢትዮጵያ አንድም ቃል አለመናገራቸው እጅግ አሳዝኖኛል ብለውል።

የሂውማን ራይትስ ዎች ተወካይ አያይዘውም በኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለውን የመብት ጥሰት ለማስቆም የሚችል አንድ የተቀናጀ ፖሊሲ ሳይኖር በተናጠል ኤርትራ ላይ ማተኮር መሞከር ሊያመጣ ከሚችለው መፍትሄ ይልቅ ሊያስከትለው የሚችል አደጋ ያመዝናል ሲሉ አስጠንቅቀዋል።

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ወያኔ የጸረ ድህነት መርሃ ግብርን ፕሮግራም ተራ የፖለቲካ ድጋፍ ለማግኘት እየተጠቀመበት ነው

ብሉ በርግ የተባለው ታዋቂ ጋዜጣ ወያኔ ከፍተኛ እርዳታ የሚያገኝበትን የጸረ ድህነት መርሀ ግብርን ተራ የፓለቲካ ድጋፍ ለማግኘት እየተጠቀመበት መሆኑን ዘገበ።

ወያኔ የተቀዋሚ ፓርቲ አባላትን በተደጋጋሚ የነፍስ አደን የምግብ እርዳታ እንደሚከለከል፣የማይክሮ ፋይናስ ብድሮችን እንዳያገኙ እና የመንግስት ስራን እንዳይሰሩ እንደሚያደርግ ብሉምበርግ መድረከን ዋቢ አድርጎ ዘግቧል።

< <አባሎቻችን ምንም እንኳን የሚሰጠውን አገልግሎት ለመጠቀም የሚያስችሉ መስፈርቶችን ቢያሟሉ በጠቅላላ ማለት ይቻላል እርዳታ እንደተከለከሉ ይታወቃል>>ሲሉ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ አንድነት መድረክ የአመራር አባል ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ ለብሉ በርግ ገልጸዋል።ፕሮፌሰሩ ሲቀጥሉም<<ይሄ ሁሉ የኢህአዴግ ነው።ለእናንተ በየነ ጴጥሮስ ያምጣላችሁ ይሏቸዋል።አባላቶቻችን የዚህ ችግር ሰለባ ናቸው።>>በማለት የወያኔን እጅግ አሳፋሪ ባህሪ የጋዜጣው ሪፓርተር ገልጿል።

በወያኔ አሳፋሪ አሰራር በጣም ከተጠቁት መርሀ ግብሮች መካከል ለሰባት ሚሊዩን አምስት መቶ ሺህ ዜጎች ምግብ እና ገንዘብ የሚረዳው የኢትዮጵያ ሴፍት ኔት ዌልፌር ፕሮግራም እንደሚገኝበት መድረክ ባወጣው መግለጫ ማስታወቁን ጠቅሶ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ከባድ የጥበቃ ስራ በሚካሄድበት አዲስ አባባ ፖሊስ ጽፈት ቤት ውስጥ የመሳሪያ ዝርፊያ ተካሄደ

የወያኔ የደህንነት፣ የመከላከያና የፖሊስ አባለት ለ24 ሰአት በተጠንቀቀ በሚጠብቁት አዲስ አበባ የመሳሪያ ዝሪፊያ መካሄዱ ፤ ዝሪፊያውም የተካሄደው በፖሊስ ጣቢያው ግቢ ውስጥ መሆኑ ብዙዎችን አስገርሟል።

ጥቅምት 24 ቀን 2002 አም ማንነታቸው ባልታወቁ ሰዎች በአዲስ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ በተፈጸመው ዝርፊያ ከ20 በላይ ክላሺንኮቭ ጠመንጃዎችና በርካታ ጥይቶችና ቦምቦች መዘረፋቸውን ምንጮቻችን ተናግረዋል። ዝርፊያው የተፈጸመው በሌሊት ሲሆን፣ የወያኔ ተረኛ ጠባቂ ፖሊሶች ስራቸውን በመስራት ላይ እንደነበሩም ለማወቅ ተችሎአል።

የዘራፊዎቹ ማንነት በውል ባይታወቅም ለዝግጅታችን ሚደርሱን መረጃዎች እንደሚያመላክቱት ዝርፊያውን የፈጸሙት ራሳቸው የወያኔ ሹመኞች ሳይሆኑ አልቀረም። የወያኔ ባለስልጣናት የተወሰኑ ፖሊሶችን ለማጥቃት በማሰብ ዝርፊያውን ሆን ብለው እንዳቀነባበሩት የሚጠቁሙ መረጃዎች በርካታ ሲሆኑ፣ የግንቦት 7 ድምጽ መረጃውን አጣርቶ ለህዝብ ይፋ ለማድረግ በመስራት ላይ ነው።

በተያያዘ ዜናም ባለፈው ወር ብቻ ከ1500 በላይ ፖሊሶች ስራቸውን በፈቃዳቸው ለቀዋል። ፖሊሶቹ ከወያኔ ጋር አብረው ለመስራት አለመፈለጋቸውን በመግለጽ የመልቀቂያ ደብዳቤ ሲያስገቡ መቆየታቸውን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን፣ ወያኔ በሚለቁ ፖሊሶች ቦታ ታማኝ ተተኪዎችን ካዘጋጀ በሁዋላ የስራ መልቀቂያውን መፍቀዱ ታውቋል። ይህን ተከትሎም ከ1500 በላይ ፖሊሶች ስራቸውን ጥለው መውጣታቸውን ከታማኝ ምንጮች ያገኘው መረጃ አመልክቷል።

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ወያኔ አገር መዝረፉ አልበቃው ሲል የግለሰቦችን ንብረት መዝረፍ ጀመረ

ከአመሰራረቱ ጀምሮ የአገር ሀብት በመዝረፍ ተወዳዳሪ ያልተገኘለት የወያኔ የሽፍታ ቡድን አሁን ደግሞ የግለሰቦችን ሀብት መዝረፍ መጀመሩን ሰሞኑን በእነዶ/ር ብርሀኑ ነጋ ቤተሰቦች ንብረት ላይ የተወሰደው እርምጃ አመላከተ

ከ25 አመት በፊት በሚሊዮን የሚቆጠሩ የትግራይ ሰዎች ተርበው የሚቀመስ ባጡበት ጊዜ ፋሽስቱ የወያኔ ዘራፊዎች ቡድን በትግራይ ህዝብ ስም የተሰበሰበውን በብዙ መቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠረውን ንብረት በመዝረፍ መለስ ዜናዊ፣ ስዩም መስፍንና አቦይ ስብሀት በግል ካዝናቸው ማስቀመጣቸውን የቀድሞ የህወሀት መስራቾች ከሆኑት መካከል አቶ ገብረመድህን አርአያ መግለጻቸው ይታወሳል። ይሄው አመላቸው አልለቃቸው ብሎ ወደ ስልጣን እንደመጡ የኢትዮጵያን ንብረት ወደ ትግራይ ሲያጓዋጉዙና በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠር ሀብት በውጭ ባንኮች ሲያጠራቅሙ መቆየታቸው በተደጋጋሚ ሲዘገብ እንደነበር ይታወቃል። የወያኔ አምባገነኖች ይህ የዝርፊያ አመል አለቃቸው ብሎ የመንግስት ንብረት የሆኑትን ፋብሪካዎች ፤ ሆቴሎችና የተለያዩ ድርጅቶችን በሽያጭ ስም በፓርቲ ወደ ሚቆጣጠሩት ንግድ ድርጅቶች በማዛወር በአንድ ምሽት ከናጠጡ ከበርቴዎች ጎራ የሚመደቡ ለመሆን የቻሉ ብቻ ሳይሆኑ በአገሪቱ አቻ የሌላቸው ሃብትማ ለመሆን መብቃታቸው የአደባባይ ሚስጥር ሆኖአል።

ይህም አልበቃ ብሎ ታዋቂ የሆኑ ባላሀብቶችን በማሰርና የንግድ ድርጅቶቻቸውንም በመቀማት ራሳቸው ባቋቋሟዋቸው ድርጅቶች እንዲያዙ ሲያደርጉ መቆየታቸው ይታወሳል። ሰሞኑን ደግሞ መፈንቅለ መንግስት ሊያደርጉብኝ ሲሉ ያዝኳቸው በማለት ከወነጀላቸው

የነጻነት ታጋዮች መካከል የተወሰኑት ንብረት እንዲታገድ ትእዛዝ አስተላልፎዋል። በትእዛዙም መሰረት የግንቦት 7 ከፍተኛ አመራሮች የሆኑት የዶ/ር ብርሀኑ ነጋና የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ፣እንዲሁም የአቶ ያረጋል ይማም፣ የአቶ ጽጌ ሀብተማሪያም፣ የጀኔራል ተፈራ ማሞ፣ የጀ/ል አሳምነው ጽጌ፣ የሌ/ል ኮሎኔል አለሁበል አማረና የአቶ ጌጡ ወርቁ ንብረቶች ይታገዳሉ። የወያኔው ልሳን በሆነው ሪፖርተር ጋዜጣ ላይ የወጣው ዘገባ እንደሚያሳየው ደግሞ እግዱ ከግለሰቦች አልፎ የቤተሰቦቻቸውንም ንብረት ጭምር ይመለከታል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## አገራቸውን ጥለው የሚሰደዱ ኢትዮጵያዊያን ቁጥር እየጨመረ መሆኑ ታዘገበ

በአገሪቱ ውስጥ እየከፋ በመጣው የኑሮ ውድነትና ባስከተለው ማህበራዊ ቀውስ ተስፋ እየቆረጡ አገራቸውን ጥለው የሚሰደዱ ዜጎች ቁጥር ከምን ጊዜውም በበለጠ እየከፋ መምጣቱ ታወቀ። በቋሚ ሰፋሪነታቸው ይታወቁ የነበሩ የደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ገጠር ነዋሪዎች ሳይቀሩ ስደት መጀመራቸውን ለማወቅ ተችሏል።

የኢትዮጵያውያን ስደተኞች ሰቆቃ እንኳንስ ለደረሰበት ለሚሰማው እንኳን አእምሮ ሊሸከመው ከሚችለው በላይ ሆኗል ይላሉ አስተያየት ሰጪዎች። በየእለቱ ሊባል በሚቻል ሁኔታ የዜና ድረ-ገፆች ሲከፈቱ የሚታዩት ርእሶች፣

## ለነፃነታችን እንኳንስ ንብረታችንን ሕይወታችንንም ለመስጠት ቆርጠን ተነስተናል!!!

ወያኔ ክፋቱን፣ ጥላቻውን እና እብሪቱን ይፋ ለማድረግ ከሚገለገልባቸው ተቋማት አንዱ "የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት" በሚል ስያሜ ይታወቃል። ይህ ተቋም በረከት ስምኦን ከሚመራቸው ቴሌቪዥንና ራድዮ የሚለየው በመድረክ ቅንብሩ፤ መግለጫ አንባቢዎቹ ካባ በመልበሳቸው እና ዜናዎቹ በበርካታ የህግ አንቀጾች የታጀቡ በመሆናቸው ነው። በተለይም "የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት" ሁለተኛ ወንጀል ችሎት የወያኔን ጨቋኝ ውሳኔዎችን ለማሳወቅ የተፈጠረ በወያኔ በእጅጉ የተወደደ፤ በሕዝብ ግን የተናቀ ተቋም ነው።

ወያኔ ሥልጣኔን ተቀናቅነዋል ብሎ እያንገላታቸው ያሉትን ወገኖቻችንንና የቤተሰቦቻቸውን ንብረት ለመዝረፍ መወሰኑ ይኸው ተቋም ጥቅምት 26 ቀን 2002 ዓ.ም. በህግ ቋንቋ በቀባባው መግለጫው ይፋ አደረገ። ተቋሙ እንደ ስሙ ፍርድ ቤት ቢሆን ኖሮ በዚህ ውሳኔ ስለተፈፀሙ በርካታ የህግና የሥነ–ሥርዓት ጥሰቶች እና ስለ ውሳኔው ፍርደ–ገምድልነት ብዙ ማለት በተቻለ ነበር። ሆኖም ተቋሙና ፍትህ የማይተዋወቁ በመሆኑ እንዲህ ዓይነት የህግ ክርክሮችን ማንሳት "ላም ባልዋለበት ..." ስለሚሆን ትተነዋል።

ይልቁንስ ወያኔ የነፃነት ታጋዮችን ንብረት መውረስ ለምን ፈለገ? በሚለው መሠረታዊ ጥያቄ ላይ እናተኩራለን። ወያኔ የጥቅምት 26ቱን የንብረት እገዳ ትእዛዝ "በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት" ተዋንያን እንዲነበብ የፈለገባቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው ብለን እናምናለን።

### በቀል

ወያኔ ሥልጣኑ አደጋ ላይ ሲወቅድ እንደቆሰለ አውሬ ያገኘውን ሁሉ ይነክሳል። በ97 ምርጫ ማግስት ታንክና ፀረ–አይሮፕላን ከተማ መሃል አስገብቶ የፈፀመውን ሁሉም የሚያውቀው ጉዳይ ነው። በመንግሥት ግልበጣ ሰበብ የያዛቸው ታጋዮችም በሥልጣኔ ላይ አድመው ነበር ብሎ በማመኑ ፍርሃቱ የወለደው ሽብር ዓይንና ጆሮ የሌለው የበቀል ውሳኔ እንዲሰጥ አድርጎታል። እነሆ በፍጹም የአውሬነት ባህርይ ወያኔ በሥልጣኔ መጥተውብኛል ብሎ በሚያምናቸው ወገኖች ብቻ ሳይሆን ቤተሰቦቻቸውንና ጓደኞቻቸውን ጭምር በመቅጣት ለመበቀል ተዘጋጅቷል። ውሳኔው በተገለፀበት እለት በተበዳዮቹ አንደበት እንደተገለፀው ሁሉ ይህ የጅምላ የበቀል እርምጃ የልጅ ልጆቻቸው ሕልውና ሳይቀር ለማጥፋት ያለመ ነው። እንዲህ ዓይነቱ የበቀል እርምጃዎች መዘዛቸው ብዙ ነው።

### አፍቅሮተ ንዋይ

ለወያኔ ንብረት ማለት ሁሉም ነገር ነው። የወያኔ መሪዎች ለገንዘብ ብለው የሚገድሉ፤ ለገንዘብ ብለው የሚሞቱ በመሆኑ ሁሉም ሰው እንደዚያ የሆነ ቢመስላቸው አይገርምም። በወያኔ እሳቤ "ለሆድ ማደር" የሰዎች ሁሉ የወል ባህርይ ነው። በዚህም ምክንያት ነው ሽልማታቸውም ቅጣታቸውም በዋናነት ንብረት ላይ ያተኮረው።

### ዋስትና ማሳጣት

የግለሰብ ንብረት ዋስትና ጥያቄ የሰብዓዊ መብት ጥያቄ አካል ነው። በመሠረቱ የግል ንብረት ዋስትና ለልማት ከሚያስፈልጉ ግብዓቶች አንዱ ነው። ወያኔ የንብረት ዋስትናን በማሳጣት ዜጎች በስጋት እንዲኖሩ እያደረገ ነው። ወያኔ ዋስትናን በመንሳት ዜጎችን ተለማማጭ አደርጋቸዋለሁ ብሎ ያምናል።

### ዘርፎ መክበርን ማበረታታት

ታታሪዎች ለፍተው ያፈሩት ሃብት ሲዘረፉ ተጎጂው መላው ማኅበረሰብ ነው። ጥሮና ግሮ ንብረት ለማፍራት መሞከር ትርፉ ከንቱ ልፋት መሆኑን በማየት ቀጣዩ ትውልድ የሥራ ተነሳሽነትን ያጣል። ሠርቶ መና ከመቅረት ዘርፎ ወይም በዝርፊያ ተባብሮ መክበር የተሻለ አማራጭ ሆኖ ይቀርባል። ለኢትዮጵያ ክፉ የሆነ ሁሉ ለወያኔ ጥሩ ነውና ሠርቶ ማደር በዘረፋ ቢተካ የወያኔ ደስታ ነው። ዘረፋና ዘራፊዎች በበዙ መጠን የሚዘረፍ ነገር እያነሰ የሚሄድ መሆኑን ወያኔዎች ገና አልተረዱትም።

### ኋላቀርነት

የኢትዮጵያን ታሪክ መለስ ብለን ስንቃኝ የሥልጣን ተቀናቃኞችን ንብረት መውረስ የዘመነ መሳፍንት ባህል መሆኑን እንረዳለን። አፄ ኃይለሥላሴም ሆነ ኮሎኔል መንግሥቱ የተቀናቃኞቻቸውን ንብረት በመውረስ አልቀለሉም። ወያኔ ከቀደሙት አንፃር ሲታይ ምን ያህል ኋላቀር እንደሆነ እዚህ ላይ ልብ ይሏል።

በግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እምነት የጥቅምት 26ቱ የንብረት እገዳ ትእዛዝ እና ወደፊት ከዚህ ጋር ተያይዘው የሚመጡ ውርሶች ፈጽሞ ተቀባይነት የላቸውም። በመሆኑም ንብረቶቹ እንደ ተዘረፉ የሚቆዩት ዘራፊዎቹ ሥልጣን ላይ እስካሉ ድረስ ብቻ ነው። ይህንን ጊዜ የማሳጠር ሥራ የሁላችንም ሊሆን ይገባል።
በዚህ አጋጣሚ ንቅናቄያችን ለየሚመለከታቸው አካላት የሚከተሉትን መልእክቶች ያስተላልፋል።

### ለጥቃቱ ግንባር ቀደም ሰለባዎች

በደረሰባችሁ ጥቃት የህመማችሁ ተካፋዮች ነን። ይህንን ዘረኛ ሥርዓት ለማስወገድ በከፈላችሁት መስዋትነት ለትውልድ የሚተላለፍ ቅርስ እንዳኖራችሁ ይሰማችሁ። የናንተ ልጆች ብቻ ሳይሆን የሁላችንም ልጆች በእናንተ የሚኮሩበት ቀን ይመጣል። ዜጎች ጥረው ግረው የድካማቸውን ውጤት ያለስጋት የሚበሉባት ኢትዮጵያ መመስረቷ አይቀሬ ነው። ያኔ ዛሬ የተዘረፈው ንብረት በክብር ይመለሳል። ያ ቀን ሩቅ አይደለም።

### ለኢትዮጵያ ሕዝብ

አምባነኖች ሰብዓዊ መብቶችን ማክበር፣ ለግል ንብረት ዋስትና መስጠትና ወገናዊ ያልሆነ የፍትህ ሥርዓት ማስፈን አይቻላቸውም። እነዚህ ሳይኖሩ ደግሞ ልማት አይኖርም። ወያኔ እስካለ ድረስ ለሕይወታችንም ለንብረታችንም አንዳች ዋስትና የለንም። አፋጣኙ መፍትሄ ራሱ ወያኔን ማስወገድ በመሆኑ ሁላችንም ኃይላችንን አስተባበረን መነሳት ያለብን መሆኑን ማስገንዘብ እንሻለን። ከዚሁ ጋር አብሮ ደግሞ የጥቃቱ ግንባር ቀደም ሰለባ ቤተሰቦች እንዳይራቡ የመርዳት የሞራል ግዴታ እንዳለብን ማስገንዘብ እንሻለን።

### ለተቃዋሚ ፓርቲዎች በሙሉ

በወያኔ መሰሪ ሴራዎች መታለል ይብቃን፤ የእርስ በርስ መናቆርም ያክትም። ራሳችንንና አገራችንን ነፃ የማውጣት የመጨረሻ ፍልሚያ ላይ መሆናችን በሁላችንም ዘንድ በቂ ግንዛቤ ይኑር። በእንዲህ ዓይነት የመረረ ወቅት ሚና መለየትና ወይ ከወያኔ አለያም ከሕዝብ ጎን መቆም ግድ ነው።

### ለወያኔ

ታጋዮቻችን ታታሪ ሠራተኞች ናቸውና ለንብረት አክብሮት አላቸው። ንብረታቸው ለፍተው ያፈሩት እንጂ እንደናንተ ለረሃብተኛ የተላከን የእርዳታ እህል ቀምተው ያጠራቀሙት አይደለም። ያም ሆኖ ግን ንብረታቸው ከነፃነታቸው አይበልጥም። እናም ንብረትን በመውረስ ቅስማቸውን መስበር አይቻላችሁም። የኢትዮጵያ ሕዝብ የፋሺስቱን ሙሶሎኒን ጦር ለመዋጋት ሲነሳ ቅሌን፣ ጨርቄን አላለም። የዛሬም ትውልድ የፋሺስቱን መለስ ዜናዊን ጦር ለመዋጋት ቅሌን፣ ጨርቄን የማይልበት ጫፍ ላይ ደርሷል። በእንዲህ ዓይነቱ ወቅት የሚደረግ መተነኳኮስ ውድቀታችሁን የሚያፈጥነው ብቻ ሳይሆን አወዳደቃችሁንም የከፋ ያደርገዋል።

የወያኔ ክፋት፣ ጥላቻና እብሪት መረን አጥቷል። ወያኔ ገንዘብ በመስጠትና ገንዘብ በመንሳት ሁሉንም ሰው መቆጣጠር የሚቻል ይመስለዋል። ለወያኔ ከንብረት የሚበልጥ ነገር የለም፤ ለኢትዮጵያዊያን ግን በምድር ላይ ከነፃነት የሚበልጥ ነገር የለም። ለነፃነታችን እንኳንስ ንብረታችን ሕይወታችንንም ለመስጠት ቆርጠን ተነስተናል።
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!

## እርማት

ባለፈው ሳምንት በቁጥር 77 ዕትማችን የመለስ ዜናዊ ለህክምና ወደ ቤልጂዬም መመላለስ ዜና መውጣት ሁለት የኤምባሲ ሠራተኞችን ከስራ አፈናቀለ በሚል አርእስት ስር አምባሳደር ብርሃኔ ገብረ ክርስቶስ ከሚሚ ስብሃቱ ጋር የአውሮፖ መዝናኛ ቦታዎችን ያስስ ነበር ተብሎ የተፃፈው ዜና ስህተት በመሆኑ ከሰሎሜ ታደሰ ጋር ተብሎ እንዲታረም በይቅርታ እንጠይቃለን።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

ሃይለ ሀሳብ

**"ንብረቱንና ቤቱን የፈለገውማ ባንዳ ሆነ፤ ለንብረቱ ለሆዱ የሚገዛ አገሩንም ይሸጣል"** **ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ**

"ንብረቱንና ቤቱን የፈለገውማ ባንዳ ሆነ፤ ለንብረቱ ለሆዱ የሚገዛ አገሩንም ይሸጣል" ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ

**ውድ አንባቢያን፡ ሰሞኑን የወያኔ ባለስልጣነት በግንቦት 7 አመራር አባላትና ለነጻነታቸው ሲታገሉ በታሰሩ ወገኖቻችን ንብረት ላይ እንደፈለጉ በሚያሸከረክሩት ፍርድ ቤት የእግድ ትእዛዝ እንዲተላለፍ አድርገዋል። ይህን ተከትሎ የግንቦት 7 ሊ/መንበር የሆኑትን ዶ/ር ብርሀኑ ነጋን አስተያየታቸውን እንዲያካፍሉን ጠይቀናቸው ነበር። እርሳቸው የሰጡት አስተያየት እንደሚከተለው ቀርቦዋልና እንድታነቡት እንጋብዛለን።**

**ጥያቄ** ፤ ወያኔ ሰሞኑን የእርስዎን፣ የአንዳንድ የግንቦት ሰባት አባሎችንና ለነጻነታቸው ሲታገሉ የታሰሩ ወገኖችን ንብረት ለመውረስ የሚያስችለውን ውሳኔ ወስኖአል። በውሳኔው ተገርመዋል?

**ዶ/ር ብርሀኑ፡** በእውነት ምንም አልገረመኝም። ይህን እንደሚያደርጉ ምንም ጥርጥር አልነበረኝም። በስልጣን ላይ ያሉት ሰዎች ሁሉንም ነገር ከንብረት ጋር እያያዙ የሚያዩ ደካማ ፍጥረቶች ናቸው። አንድን ሰው እናጥቃ ሲሉ ከምንም ነገር በላይ በንብረቱ፣ በሆዱና በቤተሰቡ ላይ ነው የሚመጡት። እንዲህ አይነቱ እርምጃ ሰውየውን ያሸማቅቀዋል፣ ለጥ ብሎ እንዲገዛ ያደርገዋል ብለው ያምናሉ። ለምሳሌ ያንን የጸረ ሽብረተኝነት አዋጅ ሲያወጡ እንዲህ አይነት እርምጃ እንደሚወስዱ ቅንጣት ታክል አልተጠራጠርኩም ነበር። 'ከአሁን በሁዋላ ይህን ህዝብ መርጦን አንገዛውም ፤ መግዛት የምንችለው አሸማቀንና ቅስሙን ሰብረን ነው፣ ቅስሙን ለመስበር ደግሞ ሁሉንም ነገር መጠቀም አለብን' ብለው ያምናሉ። ምናልባት አበሻ በሆዱ ይገዛል ብለው አስበው እንደሆን አላውቅም፣ ሁሉንም ነገር ከዘጋንበት ሰጥ ለጥ ብሎ ይገዛል ብለው ያመኑ ነው የሚመስለው።

እነኒህ ሰዎች ይህንን የጀመሩት ዛሬ አይደለም፤ ያኔ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ምምህራንን ሲያባርሩ ገና ለገና ተቃውሞ ያቀርቡብናል የሚሉትን እየመረጡ ነበር፤ በህይወታቸው በኑሮአቸውና በእንጀራቸው ነበር የመጡት ። 'የሰው ልጅ ስስ ብልት ይህ ነው፤ በእንጀራው ከመጣንበት አርፎ ይገዛል' ብለው ነው የሚያስቡት። ራሳቸው ደካሞች ስለሆኑ ሁሉንም ሰው እንደዚያ አድርጎ ከማየት የመጣ በሽታ ነውና ምንም አልገረመኝም።

**ጥያቄ፡** ውሳኔው ግንቦት 7 ለነጻነት በሚያደርገው የትግል ላይ የሚያመጣው ተጽኖ ይኖራል?

**ዶ/ር ብርሀኑ፡** አይኖርምም ይኖራልም ብየ ነው ልመልስልህ የምችለው። ምንም አይፈጥርም የምልህ ጥያቄው 'እነሱ እንዳሰቡት በንብረት ወይም በሆዳቸው እንደምንመጣባቸው ሲያውቁ፤ በግንቦት 7 ውስጥ ያሉ ሰዎች መብረክረክ ይጀምራሉ ብለው ያስባሉ' የሚል ቢሆን፣ ለዚያ መልሱ ምንም በማያወላዳ አገላለጽ በጣም ተሳስተዋል የሚል ነው መልሱ። ምክንያቱም እኛ እዚህ ትግል ውስጥ ስንገባ አይደለም በንብረታችን በህይወታችንም ቢመጣ ያለነጻነት ከምንኖር ለነጻነት ታግለን ብንሞት ይሻላል ብለን ወስነን ነው። ስለዚህ እንኳን ለገንዘብና ለንብረት ቀርቶ ለህይወታችንም ወደሁዋላ አንልም። ንብረት ማንም ሰው በነጻነት ከሰራ በቀላሉ የሚያፈራው ነገር ነው። ነጻነት ያለው ሰው ንብረት ማፍራት አይከብደውም፤ ይህ ሁሉ ኢትዮጵያዊ ነጻነት ባለበት አገር ተሰዶ ነው ራሱን ችሎ የሚኖረው ቤተሰቡንም የሚረዳው። ነጻነት ባለበት አገር የመስራት ፍላጎቱ ያለው ሰው ራሱንና ቤተሰቡን ደግፎ መኖር አያቅተውም።

በሌላ በኩል ግን 'እነዚህ ሰዎች እየሄዱበት ያለው አቅጣጫ በማህበረሰቡ ላይ እያመጣ ያለው ጉዳት እየከፋ በመሄዱ ይህ ነገር ባስቸኳይ መቆም አለበት' ስንለው የነበረውን የሚያጠናክርና ቁርጠኛነታችንን የሚጨምር ሆኖ ነው ያገኘነው። እነዚህ ነገሮች መውጣት ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ በግንቦት 7 አካባቢ የምንሰማው 'ይህ ብካይ አገዛዝ በአስቸኳይ መወገድ አለበት፤ ይህን ማህበረሰብ በነጻነቱ ማኖር የምንችለው ይህን አገዛዝ አስወግደን በቦታው የሰዎችን ህይወት የሰዎችን ማንነት የሚያከብር የህዝብ ውክልና ያለው ህዝብን የሚፈራ መንግስት መመስረት ሲቻል ነው፤ ይህም ቀስ ብሎ የሚሰራ ሳይሆን በአስቸኳይ መሰራት ያለበት ነገር ነው' የሚል ነው። እነዚህ ሰዎች ለንብረት ያላቸው እምነትና አመለካከት የግለሰቦችን ንብረት ይቅርና አገር ለመሸጥ ወደ ሁዋላ የማይሉ መሆናቸውን ከሱዳን ጋር ባደረጉት ስመምነት እያየን ነው። የአለም ማህበረሰብ ሁሉ እያወገዘ ባለበት ጊዜ፣ የኢትዮጵያን ለም መሬቶች በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ላቀረቡት የሚቸበችቡት ለገንዘብና ለንብረት ካላቸው አመለካከት የተነሳ ነው። እነዚህ ሰዎች ዛሬ አይደለም ጫካ ሆነው ከተራበው የትግራይ ህዝብ ጉሮሮ የነጠቁ ናቸው። የትግራይ ህዝብ በረሀብ ሲቆላና በቀን ከአንድ መቶ በላይ ሰዎች ሲሞቱ በነበረበት በዚያን ጊዜ፣ እነ ቦብ ጊልዶፍ ለተራበው የኢትዮጵያ ህዝብ ብለው የሰበሰቡትን ገንዘብ ለድርጅታቸው ያዋሉና ከአገር ውጭ ባሉ ባንኮች በግለሰብ ሰም ያስቀመጡ አውሬዎች ናቸው። እኔ ከምንም ተነስቼ አይደለም እንዲህ የምለው፣ በዚያን ጊዜ የህወሀት ባለሙዋሎች የነበሩ እያወጡት ያለውን ጠቅሼ ነው። ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ ተራበ ሲባል፣ ፈረንጆች እንርዳ ብለው ሲጠይቁ፣ 'የለም ስማችን ይጠፋል' ብለው 'ስማችን ከሚጠፋ በረሀብ ቢሞት ይሻላል' ብለው የሚወስኑ ሰዎች ናቸው። ግሎብ ኤንድ ሜል በተባለው ድህረ ገጽ ላይ የወጣውን የጋዜጠኛውን ጽሁፍ አይተኸው ከሆነ፣ የተራበው ሰው እንዳይታይ፣ አለም እንዳያውቅና እንዳይረዳ ለማድረግ ጋዜጠኞች ወደ ስፍራው እንዳይሄዱ አፍነው የሚይዙ፣ ከዚህ በፊት ካየናቸው ሰርአቶች የባሱ እንጅ በፍጹም የማይሻሉ መሆናቸውን ያሳዩ ሰዎች ናቸው። እና እነኒህ ሰዎች በስልጣን ላይ በሚቆዩበት በእያንዳንዷ ሰአት አገሪቱን ወደበለጠ የከፋ ችግር እየከተቱዋት የሚሄዱበት ሁኔታ ነውና ያለው፣ እኛም ሆንን መላው ህዝብ ይህንን የአራዊቶች አገዛዝ ለመጣል የአስቸኳይነት ስሜት ሊሰማው ይገባል የሚል ስሜት ነው የማየውና የምሰማው።

የኢትዮጵያን ታሪክ ያየ ሰው እኮ ይህ ነገር ከምን አይነት ጭንቅላት እንደሚወጣ ማየት አይቸግረውም። በጣሊያን ጊዜ አርበኛው ጣሊያንን ለመውጋት ጦርነት ውስጥ ሲገባ፣ ቤቱንና ንብረቱን ጣሊያን ሊወስድበት እንደሚችል ጠፍቶት አይደለም። ንብረቱንና ቤቱን የፈለገውማ ባንዳ ሆነ፤ ለንብረቱ ለሆዱ የሚገዛ አገሩንም ይሸጣል፤ እነዚህም ሰዎች የሚያስቡት እንደዚያ ነው። ግንቦት 7 ውስጥ ያለነው ሰዎች ግን በምንም አይነት ሁኔታ ከነጻነታችንና ከአገራችን ንብረትን አናስበልጥም። ለንብረት ብለን ነጻነታችንን ለማግኘት ከምናደርገው ትግል አንድ ቅንጣት ወደ ሗላ ይላሉ ብለው አስበው ከሆነ እንዲህ አይነት ውሳኔ የወሰኑት በጣም በጣም ሞኞች ናቸው።

**ጥያቄ፡** ሰሞኑን በአገር ውስጥ ከሚገኙ አንዳንድ ራሳቸውን ተቃዋሚ ብለው ከሚጠሩ ድርጅቶች ጋር ወያኔ የምርጫ ስነምግባር ስምምነት አድረጌያለሁ እያለ በማናፈስ ላይ ነው። ወያኔ ንብረት ለመውረስ እንደሚችል በጸረ ሽብር ህጉ ውስጥ እንደ ቅጣት ማካተቱ በድረድሩ ላይ ተጽኖ ነበረው የሚሉ ወገኖች አሉና የእርስዎ እይታስ ምንድነው?

**ዶ/ር ብርሀኑ፤** ይህ እኮ ካለይ የተናገርኩት ነው። ንብረት መውረስና የመሳሰሉት እርምጃዎች በአጠቃላይ ቅስምን ለመስበርና ለማስፈራራት ነው። የሽብርተኛ አዋጅ ብለው የኔ ሲያወጡ 'ተቃዋሚዎቹ ገና የአዋጁን ምንነት ሲያዩ ይደነግጣሉ' ብለው ነው ያሰቡት። አሁን የሚታየው እንቅስቃሴ አዋጁን በወሬ ብቻ ሳይሆን በተግባር እንደሚውል እናሳይ በሚል እምነት ነው። ሽብረተኛ ለመባል የሚያስፈልገው መለስና በረከት ሽብርተኛ ብለው መፈረጅ ነው። ጉዳዮችን በነጻነት አይቶ የሚፈርድ ፍርድ ቤት እንደሌለ ግልጽ ሆኗል። ስለዚህ በምርጫ እሳተፋለሁ የሚል ሁሉ እነርሱ ካሰመሩት መስመር አንድ እርምጃ እወጣለሁ ብሎ ካሰበ ያው 'ሽብርተኛ ብለው እንደሚያስሩት'፣ አስረውም ንብረቱን እንደሚወርሱት አውቆ እንዲገባ ነው ያሰቡት። እና ወደእዚህ ምርጫ የሚገባ ሰው ሙሉ በሙሉ ተሸማቆ የሚገባበትን ሁኔታ ነው የፈጠሩት። ድሮውንም ችግር የነበረበት ምርጫ በነኚህ አዋጆች ማለትም በጸረ - ሽብረተኛው አዋጅ፣ በፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና መንግስታዊ ባልሆኑ ደርጅቶች (መያዶች) አዋጅ ፈጽሞ እንዲሞት ነው የተደረገው ። የመያዶችን አዋጅ እንዳወጁ ብዙ ሳይቆዩ ነው 47 የሚሆኑ መያዶችን ያገዱት። መልእክቱ ምንድነው "የመያዶች አዋጅ በተግባር አይውልም ብለህ ካሰብክ ይኸው በተግባር ይውላል" ነው።

በጸረ ሽብረተኝነቱ አዋጅ 'ንብረት እንወርሳለን' አሉ ይኸው ተግባራዊ አደረጉት። ይህን ያየህ የምትገባበትን እወቅ ነው የሚሉት። ስለዚህ 'አርፈህ፣ ተሸማቀህና አጎንብሰህ ኑር፣ ከዚያ ውጭ ግን ነጻነት፣ ፍትህና ዲሞክራሲ የሚባል ነገር ከምር አነሳለሁ የምትል ከሆነ( ለጨዋታ ማንሳት ትችላለል ነገር ግን ከምርህ ከሆነ)እንዲሁም 'በእነዚህ ነገሮች ከልብህ አምነህ፣ ህዝብ አስነስቼ ታግየ ይህን አገዛዝ በምርጫ እጥለዋለሁ የምትል ከሆነ' ዋገህን ታገኛለህ ነው እያለ ያለው። ማንንም እስርቤት አስገብቶ ማስፈረድ እንደሚችል ያሰየበት፣ አገሩን ፍርድ ቤት የሚባል ነገር በሌለበት ጨለማ ውስጥ ነው የከተተው። እኛ የምንለው ከዚህ ጨለማ ወጥተን ብርሀን እንይ ካልን መፍትሄው መታገል ነው። በሚያውቁት፣ ለውጥ እንደሚያመጣ በምናውቀው፣ በማንኛውም መንገድ ታግለን እነኚህን ሰዎች መጣል ነው ፤ ሌላ አማራጭ የለውም እንጅ የእነሱ ስራማ 'ሰው ከአሁኑ ተንቀጥቅጥጦ ምንም አይነት ተቃውሞ እንዳያደርግ ለማድረግ ነው' የሚያስቡት።

**ጥያቄ፡** በዚህ አጋጣሚ ለነጻነታቸው ፍለጋ ሲታገሉ ለታሰሩ፤ ለነጻነታቸው ሲሉ ህይወታቸውን ለአጡት ቤተሰቦች የሚያስተላልፉት መልእክት ካለ መናገር ይችላሉ

**ዶ/ር ብርሀኑ፡** በተለያዩ ምክንያቶች ለፍትህ፣ ለዲሞክራሲና ለነጻነት ብለው በእስር ቤት ያሉ ሰዎች ( እንዲያውም እኛ ***የተዋረደው ፍርድ ቤት*** የሚል ርእስ ሰጥተን መጽሀፍ ስናወጣ መታሰቢያነቱን ያደረግነው ለእነኝህ በፍትህ እጦት ለታሰሩት ወገኖቻችን ነው)። ፍትህ ዝም ብሎ ቁጭ ብለው ስላዩት ወይም ስለፈለጉት የሚመጣ ነገር አይደለም። ፍትህዊ ስርአትን ማምጣት ትግልን ይጠይቃል። በእስር ቤት ያላችሁ ለፍትህ ብላችሁ የታገላችሁና ለነጻነታቸው ሲሉ የተሰውት ቤተሰቦች ሁሉ ፡ የእናንተ ስቃይ የእናንተ ሰቆቃ እንዲሁም የሞቱት ወገኖቻችን መስዋትነት ተደማምሮ ነው ያንን ነጻነት የሚሰጠን ። የሞቱትም ደማቸው ደመከልብ ሆኖ አይቀርም። አንድ ቀን ስማቸው በክብር ይዘከራል፤ በእስር የምትሰቃዩትም የጊዜ ጉዳይ ነው እንጅ ያቺ የታገላችሁላት ፍትህ ያቺ የታገላችሁላት ነጻነት እንደምታዩዋት አረጋግጥላችዋለሁ።ይህ አገዛዝ ጉልበት እንዳለው ለማስመሰል የሚወስዳቸው እርምጃዎች በምንም አይነት ሁኔታ ቅስማችሁን እንዳይሰብረው፤ ተስፋ እንዳትቆርጡ፣ ወገኖቻችሁ ልክ እንደናንተ ቆርጠው ይህንን በታሪካችን ታይቶ የማይታወቅ አሳፋሪ ስረአት ታግለው ለመጣል በየቦታው እየተንቀሳቀሱ ነው። የእነሱ ትግል ደግሞ ፍሬ ማፍራቱ አይቀርም ና ምንም ለአንድ ደቂቃ እንኳ ተስፋ እንዳትቆርጡ ነው የምመክረው።

## የመለስ ዜናዊ የሰብአዊ መብት አያያዝ እጅግ እየተበላሸ መሆኑን .......

ከገጽ 1 የዞረ

ይህ በዚህ እንዳለ የመንግስቱን አቋም ለዚህ ስብሰባ ለመግለጽ በተጋባዥነት ተገኝቶ የነበረው የወያኔ አምባሳደር ብርሃኔ ገብረክርስቶስ፤ በህዝባችን ላይ እየተፈጸመ ያለውን ሰቆቃ በማድበስበስ መንግስታቸው ዲሞክራሲን በአገሪቱ ለማስፈን ቁርጠኝነቱን በተግባር እየገለጸው እንደሚገኝ ነገር ግን በህዝቡ ኋላቀር ባህል ምክንያት የተፈለገውን ያህል ለመራመድ እንዳልተቻለ በመግለጽ ያደረገውን ንግግር በመቃወም በተሳታፊነት በስብሰባው አዳራሽ የተገኙት የግንቦት 7 ተወካዮችና በምርጫ 97 ወቅት የኦሮሞ ፈደራሊስትን በመወከል ፓርላማ ገብተው የነበሩት የፓርቲው ዋና ጸሃፊ ዶ/ር ጌታቸው ጂጊ በየተራ ባሰሙት ተቃውሞ በመደናገጥ ስብሰባውን አቋርጦ ለመውጣት እደተገደደ ተያይዞ የደረሰን ዜና ያስረዳል። የወያኔ ፋሽስታዊ የሰብአዊ መብት ጥሰት እንዳይነሳ ለመከላከል የስብሰባውን የውይይት አቅጣጫ ወደ ኢትዮ ኤርትራ የድንበር ውዝግብ ለማዞር ሞክሮ የነበረው ብርሃኔ ገብረክርስቶስ የኤርትራ ሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ነን ካሉት ሳይቀር ከፍተኛ ተቃውሞ ሰለገጠመው አሳ ጎርጓሪ ዘንዶ ያወጣል እንዲሉ ኢትዮጵያ በአስቸኳይ የአለም አቀፉ የድንበር ኮሚቴ የወሰነውን ውሳኔ ተግባራዊ እንድታደርግ የሚጠይቅ አቋም በወጣው መግለጫ እንዲካተት ለማስደረግ ችሎአል። ኤርትራ አልሸባብን በመርዳት በሱማሌ ውስጥ ያለው ሁኔታ እንዳይረጋጋ እንቅፋት ፈጥራለች በማለት የወያኔው አምባሳደር ያቀረበውንም ክስ ኤርትራዊያኑም ሆኑ በስብሰባው ላይ በተጋባዥነት የተገኘው የሱማሌ ተወካይ ያጣጣሉት ሲሆን እንዲያውም የኢትዮጵያ ወረራ ለአልሸባብ በክልሉ መፈጠር ምክንያት ሆኖአል የሚል መራር ትችትና ውግዘት አስከትሎበታል።

‘የመለስ አገዛዝ ምዕራባዊያን የዕርዳታ ለጋሾችን ለማታለል ሰለ ዲሞክራሲና ሰብአዊ መብት የሚያደርገውን ድስኩር ድህረ ምርጫ 97 በንጹሃን የአዲስ አበባ ሰላማዊ ሠልፈኞች ላይ የወሰደው ጭፍጨፋ ይበልጥ አጋልጦታል፤ የአምባሳደሩ ንግግርም እርሱ እና እርሱ የሚወክለው መንግሥት ላለፉት 18 አመታት የተካኑበት ቅጥፈት አካል ስለሆነ በተግባርና በወሬ መካከል ያለውን ልዩነት አድማጭ አይቶ እንዲፈርድ በመለስ ዜናዊ ቀጥተኛ የዕዝ ሰንሰለት ሥር የነበረው ሠራዊት ግንባር ግንባራቸውን በጥይት ቦርጭቆ ከገደላቸው ውስጥ ለአብነት ይዘን የመጣነውን ዘግናኝ ፎቶግራፎች የስብሰባው ተሳታፊዎች እንድትመለከቱልን እንጠይቃለን“ በማለት የግንቦት 7 ተወካይ ጥያቄ ለመጠየቅ ባገኙት አጭር እድል ለስብሰባው አንደተናገሩ ዶ/ር ጌታቸው ጂጊ ለጥቀው ,‘ሴት እህቶቻችን ብልት ውስጥ የጋለ ብረትና ጠርሙስ እየከተተ አረሜኔያዊ ድርጊት የሚፈጸመው መንግሥት ተወካይ በዚህ ስብሰባ ላይ የመናገር ሞራላዊ ብቃት የለውም‘ በማለት እልህ የተሞላበት አስተያየት ሰጥተዋል ። ወትሮ ወደሚሄድበት ቦታ ሁሉ በአንድ ወይም ሁለት የበታች ሠራተኞች ታጅቦ ሲሄድ ይታይ የነበረው ከፍተኛ የወያኔ ሹም ፤ተቃዋሚ ይገጠመኛል ብሎ ባለማሰቡ ይመስላል ብቻውን ዘና ብሎ በመጣበት ስብሰባ የደረሰበትን ውርደት ለመሸሽ ስቁነጠነጥ ከአጭር የቡና ዕረፍት ቦኋላ ውይይት ይደርግበታል የተባለውን በአብዛኛው በርሱም ንግግር ክፍል ውስጥ ,‘መሻሻል ተደርጎበታል‘ በማለት የቀረበው የሰብአዊ መብት ጉዳይ ውይይት ሳይጀመር የተገኘውን አጋጣሚ በመጠቀም እግሬ አውጭኝ ብሎ አንደተሰወረ ዘጋቢያችን ገልጾአል።

## ወያኔ የጸረ ድህነት መርሃ ግብርን ፕሮግራም ተራ የፖለቲካ ድጋፍ ለማግኘት

ከገጽ 1 የዞረ

ብሉ ብርግ ዘግቧል። የዩንቨርሲት ምሩቃን የመንግስት ስራ ለማግኘት ወይም መምህራን ለመሆን የወያኔ አባልነት ቅጽ መሙላት እንዳለባቸው የተገለጸ ሲሆን፣ ወያኔ አባላቴ ካልሆናችሁ በመምህርነት አልቀጥራችሁም የሚልበት የትምህርት ስርአት የሚደጎመው በአዎሮፓዊያን የእርዳታ ኤጀንሲዎች መሆኑም ተዘግቧል።

በተመሳሳይ ዜና ሮይተርስ የተቋዋሚ ፓርቲ አባላት የእርዳታ እህል መከልከላቸውን እና ክልከላው የተደረገው አባላቱ በግንቦት ከሚደረገው ምርጫ ተብዩ ድራማ በፊት ወያኔን እንዲቀላቀሉ ታስቦ መሆኑን የኢትዮድያ ፌዴራላዊ አንድነት መድረክ ቃልአቀባይን ጠቅሶ ዘግቧል።

<<አባላቶቻችን ምግብ ለስራ በተባለው መርሀግብርም እንዳይሳተፉ ተከልክለዋል>>ያሉት የመድረክ ቃል አቀባይ አቶ ገብሩ አስራት ናቸው።ሲቀጥሉም<<የወያኔ አባላት ብቻ ናቸው በመርሀግብሩ መሳተፍ የሚችሉት።ይህም የተደረገው በጣም የተቸገሩ ሰዎች የተቋዋሚውን ጎራ ትተው ወደ ወያኔ እንዲሄዱ ነው>> ብለዋል። በርከት ስምኦን ከሮይተርስ የቀረበለትን ጥያቄ በውሸት በሰለጠነው አንደበቱን እና በተለመደው ወያኔያዊ ድርቅና ሸምጥጦ መካዱ ታውቋል።

## ከባድ የጥበቃ ስራ በሚካሄድበት አዲስ አባባ ፖሊስ ጽፈት ቤት ውስጥ የመሳሪያ ዝርፊያ ተካሄደ

ከገጽ 1 የዞረ

ወያኔ በፖሊሶች ላይ ያለው ጥርጣሬ በየጊዜው እየጨመረ በመምጣቱ በቅርቡ በጠላይ ወታደራዊ ማስልጠኛ ጣቢያ ግምገማ አካሄዶ በርካታ ፖሊሶችን ማባረሩ የሚታወስ ሲሆን፣ ተመሳሳይ ዙር ግምገማ በቅርቡ እንደሚደረግም ለማወቅ ተችሎአል።

ወታደሮችና ፖሊሶች አገርን በመግደል ላይ ካለው የወያኔ አገዛዝ ጋር በመተባበር ወገናቸውን ከመበደል እንዲታቀቡና የነጻነት ሀይሎችን እንዲቀላቀሉ የግንቦት 7 ሊ/መንበር የሆኑት ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ በአዲስ አመት መልእክታቸው ጥሪ ማቅረባቸው የሚታወስ ሲሆን፣ ጥሪው በሰራዊቱና በፖሊሶች ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት እያገኘ መምጣቱን የሚደርሱን መረጃዎች ያሳያሉ።

## ወያኔ አገር መዝረፉ አልበቃው ሲል የግለሰቦችን ንብረት መዝረፍ ጀመረ

ከገጽ 1 የዞረ

ወያኔ እንዲታገዱ ካደረጋቸው ድርጅቶች መካከል የዶ/ር ብርሀኑ ቤተሰቦች ንብረት የሆኑት ነጋና ቤተሰቡ ሀ/የተ/የግል/ማ፣ አዲስ መንገድ የቤት ስራ አክሲዮን ማህበር፣ የኢትዮጵያ የበቆሎና የእርሻ እንዱስትሪ ማህበር፣ አዲስ ብሮድካስቲንግ ኩባንያ፣ ፈውስ የመድሀኒት ፋብሪካ፣ አርቢት የቤተሰብ አንቶሜቲክ የአይን ህክምና ክሊኒክና የአይን መድሀኒቶች አስመጭና ችርቻሮ ይገኙበታል። የወያኔ እርምጃ አገዛዙ ምን ያክል ተስፋ እየቆረጠ፣ በግንቦት 7 እንቅስቃሴም እየተደናገጠ መምጣቱን ያሳያል የሚሉ በርካታ አስተያየቶች ለግንቦት 7 ደርሰዋል።

ሰሞኑን ከደረሱን የስልክ መልእክቶች መካከል አብዛኞቹ ለዶ/ር ብርሀኑና ለቤተሰቦቻቸው ያላቸውን ድጋፍ የሚገለጹ መሆናቸውን ለመረዳት የተቻለ ሲሆን፣ ወያኔ በቆራጥ የኢትዮጵያ ልጆች ተሸቀንጥሮ ሲወድቅ አሁን የተዘረፈው ሀብት ሙሉበሙሉ እንደሚመለስላቸውም ያላቸውን ጽኑ እምነት ገልጸዋል።

ከዶ/ር ብርሀኑ ቤተሰቦች ንብረት ሌላ የሌሎች የነጻነት ታገዮች ንብረት የሆኑ መኖሪያ ቤቶችና ድርጅቶችም እንዲታገዱ ትእዛዝ መተላለፉ ሲታወቅ፣ ወያኔ በታጋዮች የአቋም ጽናት እየተሸበረ በመምጣቱ ጥቃቱን ወደ ቤተሰቦቻቸው ለማዞር መገደዱም ታውቋል።

## አገራቸውን ጥለው የሚሰደዱ ኢትዮጵያዊያን ቁጥር እየጨመረ መሆኑ ታዘገበ

ከገጽ 1 የዞረ

“ወደ የመን ሊያቋርጡ ሲሞክሩ የነበሩን ኢትዮጵያውያን ተሸከማ የነበረች ጀልባ ሰጠመች፤ የግብጽ ፖሊስ ወደ እስራኤል ለማቋረጥ ሲሞክር የነበረን ኢትዮጵያዊ ተኩሶ ገደለ፤ የማላዊ ፖሊስ 60 ኢትዮጵያውያን ስደተኞችን አሰረ፤ ከሁለት ሺህ የሚበልጡ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች በታንዛኒያ እስር ላይ ይገኛሉ፤ 80 ኢትዮጵያውያን ሴቶች በቤይሩት እስር ቤት ውስጥ ያለጠያቂ ናቸው፤ ኢትዮጵያውያን ኢራቅ ውስጥ ስራ ይፈልጋሉ፤ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች በደቡብ አፍሪካ ተደበደቡ፤ ኢትዮጵያዊት ሰራተኛ በአንድ የመካከለኛ ምስራቅ አገር ተገደለች፤ የሚሉ እና የመሳሰሉት ናቸው።

ይህ ዜና በተጠናቀረበት በዛሬው ቀን እንኳ የየመን ፖሊስ በህገ-ወጥ መንገድ የገቡ ብዙ ኢትዮጵያውያንን አግቶ ያለ መሆኑን የሚያሳዩ ዜናዎች በየድረ-ገፆች ላይ ተለጥፈዋል። ስደት የኢትዮጵያውያን የእለት ተእለት ሕይወት እውነታ ሆኗል። ኢትዮጵያውያን ያላቸው ምርጫ ወይ አገራቸው ውስጥ ሆነው መራብ፣ ስራ ማጣት፣ መታሰር፣ ተገዶ እና ተዋርዶ የፓርቲ አባል መሆን አለያም መሰደድ እና እድልን መሞከር ብቻ ሆኗል።

የፋሽስቱ መለስ አገዛዝ በየአመቱ ባለሁለት አሃዝ የኢኮኖሚ ዕድገት አስመዝግቤያለሁ እያለ ልማታዊ መንግሥት መስሎ ለመታየት፤ በተለይም እርዳታ ለጋሽ የሆኑትን የምዕራቡን አለም መንግስታትና የገንዘብ አበዳሪ ተቋሞቻቸውን በተጭበረበረ እና በተፈበረከ መረጃ ለማሳመን ደፋ ቀና ከሚልበት የምርጫ 97 ቀውስ ወዲህ እየተባባሰ በመሄድ ላይ በሚገኘው የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ድቀት ችግር ምክንያት ተስፋ የጨለመባቸው በርካታ ወጣቶች ህይወታቸውን ለከፍተኛ አደጋ የሚያጋልጥ ሃላፊነት በመውሰድ ወደ ደቡብ አፍሪካ እና አረብ አገሮች ያደርጉት ከነበረው ጉዞ በተጨማሪ፤ ቀደም ሲል ለተሻለ ኑሮ ፍለጋ ተኪዶበት ወደማይታወቀው ሱዳን አገር ጭምር መፍለስ መጀመራቸው ታውቆአል።

በአገሪቱ ውስጥ ያለው የኑሮ ሁኔታ የከፋ ደረጃ ላይ መድረሱን ከሚያስረዱት ክስተቶች ውስጥ፥ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ የገጠር ነዋሪዎች ሳይቀሩ መሰደድ መጀመራቸው እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል። ደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ አስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ይከሰቱ በነበሩት ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ችግሮች የሚፈናቀሉትን ለማስተናገጃነት /ለሰፈራ ቦታነት/ ይውል እንደነበር ይታወቃል።

ኢትዮጵያውያን በብዛት አገራቸውን ጥለው መሰደድ የጀመሩት አምባገነናዊው የደርግ ስርአት ስልጣን ከያዘ በኋላ ከፖለቲካ ጋር በተያያዘ ይደርስባቸው የነበረውን አደጋ በመሸሽ እንደሆነ ና ይህም ባብዛኛዉ የአገዛዙን ኢፍትሃዊና አድሎአዊ አሰራር ለመቃወም እውቀቱና ድፍረቱ የነበረው በአብዛኛው የተማረውን የህብረተሰብ ክፍል የሚመለከት ሲሆን በዛም ከተባለ በንፅጽር የፖለቲካ ንቃቱ የተሻለ ደረጃ ላይ ነበር የሚባለውን ከተሜ የሚጨምር ነበር።

በአገራችን ታሪክ አብዛኛው ገጠሬ፣ በተለይም ለም በሆኑ የደቡብ ምእራብ አካባቢዎች የሚኖረው ቀዬውን ለቆ ርቆ መሄድን አልለመደም። አሁን ግን፤ የደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ገጠር ገበሬዎች ወንዶች እና ሴቶች ቀዬያቸውን እየጣሉ ወደ ሱዳን እና ደቡብ አፍሪካ ማዝገም መጀመራቸው የወያኔ የፓለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ፖሊሲዎች ውጤት መሆኑ ራሳቸው ገበሬዎች እየተናገሩ መሆኑን የግንቦት 7 ዘጋቢ ተረድቷል።

በአካባቢው ያሉ ምንጮችን በማነጋገር መረጃ የሰበሰበው የግንቦት 7 ዘጋቢ፥ በሱዳን እና ደቡብ አፍሪካ የቀን ሰራተኞች እና የቤት ሰራተኞች የሚከፈለውን ደሞዝ በዘመድ አዝማድ ሰዎች የሚያወሩትን የሰሙ ሴቶች እና ወንዶች አደገኛ የእግር እና የመኪና ጉዞዎችን በማድረግ ድንበር ማቋረጥ እንደጀመሩ ተረድቷል። ምንም እንኳ በስደተኞች ላይ የሚደርሰውን እስከሞት የሚደርስ አካላዊ እና የተለያዩ ጉዳቶች በሰላም ከደረሱት በደብዳቤ እና በወሬ ቢሰማም፤ ይህ ግን ሌሎችንም መውጫ ከመፈለግ እንዳልከለከላቸው ለማወቅ ችሏል።


# የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ

## የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

በ17870 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ19610 KHZ በ31 ሜትር ባንድ ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን።**

g7radio@ginbot7.org